# በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግሥት

# የንግድና ኢንደስትሪ ልማት ሴክተር

## የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ድጋፍ ሜቀሮች አፈጻጸም ክትትል
## ዋና ስራ ሂደት

## የ2009 በጀት ዓመት የ 9 ወር ዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርት

መጋቢት /2009

<u>ሀዋሣ</u>

መግቢያ

በሁለተኛው ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ወቅት የኢንዱስትሪው ዘርፍ የሜነት ሜወጓ በክልላችን እንዲጫወት ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ተግባራት በሒናወን ላይ ማሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም በእስከአሁኑ ሂደት በስራ ሂደቱ የ2009ዓ.ም በጀት ዓመት ዕቅድ በማዘጋጀትና በየደረጃው ከሚገኙ ፈጻሚዎችና የዘርፉ አሜራር ጋር በመወያየትና የጋራ ግንዛቤ በማያዝና በሜፈራረም ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በዚህም የ9 ወር ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ድጋፍ ሜቀፎችና አፈጻጸም ክትትል ዋና ስራ ሂደት አንፃር ከክልል እስከ አንድ ሜከል ደረስ የተከናወኑ ተግባራትን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተችሏል፡፡

## ክፍል አንድ

## 1.በኢንተርፐራይዞች ግንባር የማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪ ዘርፍ አዝማሚያዊ ግምገማ

### 1.1. በዘርፉ ሁለገብ ሰራዊት ከማንባት አንጻር

የዘርፉ አሜራር ራሱ የሰራዊቱ አንድ አካል እንደማሆኑ በአማካከት፣ በክህሎት፣ በተግባር አፈጻጸምና አደረጃጀት ረገድ የሚገኙ ጥንካሬዎች ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሜድረግ፣ የሚስፋት እንዲሁም በዚሁ ሂደት የሚታዩ ክፍተቶችን መሙላት፣ አደረጃጀቶቹን ተጠቅሞ ስራዎችን በቁርጠኝነት እየገማመ ማምራት ያለበት ማሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በማሆኑም በበጀት ዓመቱ ከተጣሉ ቁልፍ ግቦች መካከል አንዱ የልማት ሠራዊት ግንባታ ግብ ማሆኑን ታሳቢ በሜድረግ ዝግጅት ሜደረጉ ይታወቃል፡፡

በዚሁ ማሰረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪ ዘርፍ ከልማት ሠራዊት ግንባታ ግቦች አንፃር የተከናወኑ ተግባራትን ከእያአንዳንዱ የሰራዊቱ አካላት (3ቱ የልማት አቅሞች) አንጻር እስከዚህ ዘጠኝ ወር የተደረጉ እንቅስቃሴዎች አፈፃፀም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በማንግስት ክንፍ የተፈጠረ አደረጃጀትን በተማከተ በዘርፉ በክልል 3 እና በታችኛው መዋቅር 277 በድምሩ 280 የለውጥ ቡድን አደረጃጀቶች እንዲሁም በክልል 6 እና በታችኛው መዋቅር 309 በድምሩ 316 የ1ለ5 አደረጃጀቶች ተፈጥረው በተቀማጠው አቅጣጫ መሠረት በአጀንዳዎቻቸው ዙሪያ ወይይት አድርገዋል፡፡
- በዚሁ ማሰረት ከ280 የለውጥ ቡድኖች ወስጥ 189 የለውጥ ቡድኖች በደረጃ ተለይተው ፊት የወጣ 97፣ መሀል ያለ 89 እና 2 ኋላ የቀረ በማለት የተለዩ ሲሆን ከ315 የ1ለ5 አደረጃጀቶች ወስጥ 300 የ1ለ5 አደረጃጀቶች በደረጃ ለማለየት ተሞክሮ 142 ፊት የወጣ፣ 156 መሀል ያለ እና 2 ኋላ በቀረ የተፈረጁ ማሆኑን ለሚረጋገጥ ተችሏል፡፡

**የህዝብ ክንፍ አደረጃጀትን በተማከተ፡**-በአጠቃላይ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በ **5,610** የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የታቀፉ **29,207** አንቀሳቃሾች **4,814** የ1ለ5 አደረጃጀቶች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም መካከል **3,341** የ1ለ5 አደረጃጀቶች ተመዝነው **2,117**ፊት የወጣ፣ **1,112**መሀል ያለ እና **112** 1ለ5 ቶች ኋላ በቀረ ደረጃ የተለዩ ሲሆን ቀሪዎቹ አደረጃጀቶች ግን በደረጃ ያልተመዘኑ ናቸው፡፡ በክልሉ በአጠቃላይ በቅርቡ በተደረገው አጠቃላይ ቆጠራ የኢንዱድትሪያሊስቱ ቁጥር **10875** ሲሆን ከላይ ከተደራጁት ውጭ ያሉት በቀጣይ ወደ አደረጃጀት የሚታቀፉ ይሆናል፡፡

- 1,673 የምርታማነትና ጥራት ቡድኖች ተደራጅተው በየአጀንዳዎቻቸው መደበኛ ወይይታቸውን በየወቅቱ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከደረጃ ፍረጃ አንጻር ሲታይ 1,123 የተማዘኑ ሲሆን 554 ፊት የወጡ፣ 486 መሀል ያለ እና 83 ኋላ በቀረ የተፈረጁ ሲሆን 550 ኢንዱስትሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ያልተማዘኑ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ቆጠራው እንደተለየው በአደረጃጀት ያልተካተቱ ኢንዱስትሪያሊስቶች ያሉ በመሆኑ በቀጣይ እነዚህን በማካተት አደረጃጀቶችን ማጠናከርና አዳዲስ አደረጃጀቶችን የመፍጠር ሥራ ማሰራት ይኖርበታል፡፡

## ህለገብ ሰራዊት ከመገንባት አንጻር በጥንካሬና በጉድለት የተለዩ ዋና ዋና ጉዳዮች

### በጥንካሬ

- የሰራዊቱ ክንፎች በየወቅቱ ከተልኳቸው ጋ ሻ እየተወያዩ በትግል ደረጃ እየሰጡ መምጣታቸውና በዚህም ግንባር ቀደሞች መፍጠርና ማለየት በመቻሉ የግንባር ቀደም አንቀሳቃሾች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ፣
- የተለያዩ የማነበረሰብ ክፍሎችን በማወያየትና የጋራ መግባባት በመፍጠር የህዝብ ክንፉ ማ ቆዎችን በማለየት ከመንግስት ክንፉ ጋር በቅንጅት ማሰራት መጀመራቸው፣
- እስከ አሁን በዘርፉ ተዋናዮች ላይ በተሰራው የአመለካከት ቀረጻ ስራ ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ዘርፉ የሚቀላቀሉ አዳዲስ ተዋናዮች/አንቀሳቃሾች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ከሌሎች ዘርፎች ወደ ማኑፋክቸሪንግ የሚደረገው ሽግግር ለውጥ በማሳየቱ የማኑክቸሪንግ ተቋማትን ከመጨመር አንጻር በ9 ወሩ ከእቅድ በላይ ሊከናወን ችሏል፡፡
- የአምራቾቹ ምርትና ምርታማነት ለመጨመርና በገበያ ተወዳዳሪ ለመሆን የማሽነሪ ፋይዳ የላቀ መሆኑን በየደረጃውና በየአደረጃጀቱ በተሰራው የግንዛቤና የአመለካከት ቀረጻ ስራ የማሽነሪ ፍላጎት እየጨመረ ከመምጣቱም በላይ የቀረቡ ማሽነሪዎችን ሙሉ ፓኬጅ የመወሰድና ቀሪ ቅድመ ክፍያ ከመክፈል አንጻር የተሻለ የአመለካከት ለውጥ በተጨባጭ መጥቷል፡፡ ይሁንና የካፒታል ዕቃ አቅራቢ ተቋማት፣ በኃይል አቅርቦትና ሌሎች ማሰረተ ልማቶች መሟላት አንጻር የሚታዩ ማ ቆዎች ዛሬም የህዝብ ክንፉ በየ ወይይት መድረኩ የሚያነሳቸው የመልካም አስተዳደር ችግር አጀንዳዎች በመሆናቸው ባለድርሻ አካላቱ አፋጣኝ መፍትሔ ሊያበጁለት ይገባል፡፡
- በክልላችን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሥራ ማስኬ የተሰማሩና የሚሰማሩ ኢንዱስትሪያሊስቶችን የማሽነሪ ሊዝ ተጠቃሚዎች ለማድረግ ብር 192,342,858 የመሳሪያ ሊዝ ብድር ለማቅረብ በእቅድ በተያዘው ማሰረት በደቡብ ካፒታል ዕቃዎች አቅራቢ አ/ማ የብር 25,322,501 የሚገመት የብድር ጥያቄ የያዘ 186 የንግድ ሥራ ዕቅድ የቀረበ ሲሆን ከዚሁ ወስጥ 159 የተለያዩ ማሽነሪዎች ተገዝተው በትራንስፖርት ሂደት ላይ ሲሆኑ በአሁን ሰዓት በወልቂጤ፣ በቡታጅራ፣ በወራቤ፣ አረካ ከተሞች… ከዚህ በፊት በከፍተኛ ሁኔታ የመልካም አስተዳደር ችግር ሆነው ሲነሱ የነበሩ ችግሮች ምላሽ እየተሰጠ መሆኑና ቀሪ ማሽነሪዎች በግዢ ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡
- በኢትዮጵያ ልማት ባንክ 1,702,909,913 ብር የብድር ጥያቄ የያዘ 272 የንግድ ሥራ ዕቅድ የቀረበ ሲሆን ከዚህም ወስጥ 516,669,598 ብር የሚገመት የብድር ጥያቄ የያዘ 83 የንግድ

ሥራ ዕቅድ ጸድቋል፡፡ ቀሪዎቹ 189 የንግድ ሥራ ዕቅዶች በተለያየ ሚልኩ የማጣራትና አስፈላጊ ማስፈርቶችን በማሟላት ሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን በልማት ባንክ በኩል አራት ማሽነሪዎች (በይርጋለም ከተማ ሁለት ማሽነሪ በአግሮፕሮሰሲንግ ዘርፍ የዱቄት ፋብሪካዎችና በሚዛን አማን ከተማ ሁለት ማሽነሪዎች በኮንስትራክሽን ዘርፍ የብሎኬት ማምረቻ) ቀርበው የተተከሉ ሲሆን ቀሪ ሁለት ማሽነሪዎች ለአለታ ወንዶ ከተማ አንድ የዱቄት ፋብሪካ ቀርቦ በተከላ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም አንድ የስቲኪኒና አንድ የስቴፕለር ፋብሪካ ማሽነሪዎች በትራንስፖርት ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

- ከዞን ማዕከል የሚሉኩ አፈጻጸሞች በስራቸው የሚገኙትን የከተሞች የወረዳ አፈጻፀም ደረጃ ተገምግሞ እየተፈረጀ መላክ መጀመራቸው፣
- ኢንዱስትሪያሊስቶች በሚወስዷቸው ማሽነሪዎች ዙርያ የጠራ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና የመግዛትና የመጠቀም አቅምና ፍላጎታቸውን ያማከለ እንዲሆን ለማስቻል በ9 ወሩ ከመካሪያ ሊዝ አቅራቢ ተቋማት የሚቀርቡ የማሽነሪ ዝርዝሮችና ስፔስፊኬሽኖችና ካታሎጎችን ከሊዝ ኩባንያወና ከተለያዩ ኢንስቲቲዩቶች ጋር በመቀናጀት በማዘጋጀት ለታችኛዉ መዋቅር እንዲደርስና ማሽነሪዎቹ ከመምጣታቸው በፊት ኢንዱስትሪያሊስቶቹ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል፡፡ ለአብነትም በእንጨትና ብረታብረት፣ በቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ በጨርቃጨርቅና አግርፕሮሰሲንግ ዘርፎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- የብረትና የእንጨት ማሽነሪዎችን በተመለከተ የኮሚሽንግ ስራዎችንና ስልጠና ለማስጠት በተያዘው የጋራ ዕቅድ ማካረት ወልቂጤ፣ ቡታጅራ፣ ወራቤ፣ ሆሳዕና፣ ሀላባ፣ ሀዋሳ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ ( በክላስተር ማዕከላት ያሉ)፣ ማሻ፣ አረካ፣ ቦዲቲ፣ ሚዛን አማን፣ አለታ ወንዶ ከተሞች የኮሚሽኒንግ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን የሀይል አቅርቦት ችግር በመኖሩ ምክንያት የኮሚሽኒንግ ሥራ ቢከናወንም ወደ ሥራ ያልገቡ ከተሞች አርባ ምንጭ የብረታብረት ብሎክ፣ ተርጫ ጂንካ፣ ቦዲት፣ ይርጋጨፌ፣ ማሻ፣ ሚዛን አማን፣ ሳወላ፣ ወላይታ ሶዶ (በግል ሥራ ማዕከላት የተተከሉ) ከተሞች እስካሁን ወደሥራ ሊገቡ አልቻሉም፡፡ በሌላ ሚልኩ ቀረበና በሊዝ ሥርዓት ያልተላለፉ ማሽነሪዎችን ፍላጎት ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ የረገኛል፡፡
- በ9 ወሩ አምስቱን ፍሌክሰብል ዎርክሾፖች በመደገፍ በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ለማስቻል የድጋፍና ክትትል ሥራ የተሰራ ሲሆን በሂደቱም ከፍተኛ የሆነ የገበያ፣ የክህሎት፣ የአመላካከትና የንግድ ሥራ አመራር በተለይም የሀብትና ፋይናንስ አጠቃቀም ችግሮች መኖራቸውን ለማየት የተቻለ ሲሆን ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ጥረት ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የፋይናንስ ችግሮችን ለመቅረፍ ከኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ ጋር በመቀናጀት የተፈታ ሲሆን በሊዝ ፋይናንስ ስርዓት የንብረት ማስተላለፍ ሥራ በደቡብ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ/ማኅበር በኩል ተከናወኗል፡፡ የገበያ ችግሮችን ለመፍታት የገበያ አማራጮች ልየታ በማከናወንና የገበያ ድጋፍ ማዕቀፍ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለማስጸደቅ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በሴክተሩ የተለዩ ችግሮች በጋራ የሚፈቱበትን አግባብ ለመፍጠር ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያካተተ የጋራ የምክክር መድረክ (የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር) ለማዘጋጀት ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል፡፡

- ወቅቱን ጠብቆ የ9 ወር ሪፖርት ወደ ክልል ማዕከል ከማላክ አንፃር ጋሞጎፋ፣ ጉራጌ፤ ሥልጤ፣ ከፋ፤ ሀዋሣ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ዳወሮ፣ ሰገን አካባቢ ሕዝቦች፣ ቤንች ማጂ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ የም፣ ሀላባ፣ ባስኬቶ ልዩ ወረዳ በወቅቱ ሪፖርቶችን የላኩ ሲሆኑ ጌድኦ፣ ወላይታ፣ ሸካ ዞን ሪፖርት አዘግይተው ልከዋል፡፡ ኮንታ ልዩ ወረዳ ሪፖርት አልላከም፡፡

**በጉድለት**

- ሶስቱም የሰራዊት ክንፎች በየአደረጃጀቶቻቸው የሚያደርጓቸው ወይይቶች መሻሻል ያሳዩ ቢሆንም በችግሮች ዙሪያ በጥልቀት ተወያይቶ መፍትሄ ከሚፈለግና የተሻሉ አፈፃፀሞችን ከማስፋትና ከማስቀጠል አንጻር አሁንም ከጉድለት ያልተላቀቁ መሆኑና ያላቸወን ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ሙሉ በሙሉ ፈርጀው ያለማላካቸው፤
- ለ 5ቱ ፍሌክሰብል ማኑፋክቸሪንግ ዎርክሾፖች (ዲላ፣ ሀዋሳ፣ ሶዶ፣ ሆሳዕናና አርባምንጭ) በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላት ከገበያና ፋይናንስ ድጋፍ አንጻር በቂና ችግር ፈቺ ድጋፍ ከማስጠት አንጻር ሰፊ ጉድለት የሚስተዋል ሲሆን የተደራጁትን ጨምሮ በአንዳንድ መዋቅሮች የሚገኙ የዘርፉ ተዋናዮች ዘንድ በምርታማነትና ጥራት ተወዳዳሪ በመሆን በገበያ አሸናፊ ሆኖ ከመቅረብ ይልቅ አሁንም የመንግስትን የገበያ ድጋፍ ብቻ የማጠበቅ አማላካከት በተገቢው ያልተቀረፈ መሆኑ፡፡
- በአደረጃጀቶች ወይይት የመቆራረጥ፣ ሪፖርትና ግብረ መልስ በወቅቱ ያለማቅረብ፣ የተደራጀና የጠራ መረጃ በብቃት ያለማቅረብ (በመንግስት ክንፉ)፤ ለሁሉም የዘርፉ ተግባር እኩል ትኩረት ሰጥቶ ያለመንቀሳቀስ፣ በአጀንዳዎች ዙሪያ ጥልቀት ያለው ወይይት ከማድረግ አንጻር በበርካታ መዋቅሮች አካባቢ ጉድለት ያለው መሆኑ ተገምግሟል፡፡

## 2. በመልካም አስተዳደር እርካታን ከማረጋገጥ አንፃር

መንግስት ትኩረት አድርጎ ከሚንቀሳቀስባቸው ጉዳዮች አንዱ ልማታዊ መልካም አስተዳደር የማስፈን ሥራ ነው፡፡ የመልካም አስተዳደር ትግል ጉዳይ የአማራጭ ጉዳይ ሳይሆን ለሰላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የሕልወና ጉዳይ በመሆኑ በዘርፉ የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በተደራጀ ልማት ሰራዊትና በምልዓተ ህዝቡ ተሳትፎና በንቅናቄ ለመፍታት በቢሮ ደረጃ በበጀት ዓመቱ በሴክተሩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ መንስኤያቸው፣ ችግሮቹን የሚፈቱበት ጊዜ፣ በማንና እንዴት እንደሚፈቱ በተዘጋጀው ሰነድ ላይ በጥልቀት በመወያየትና እንዲዳብር በማድረግ በታችኛወም መዋቅር ዘንድ በተመሳሳይ እንዲፈጸም በመደረጉ እንዲሁም በዓመታዊ የግብ ስምምነት ወቅት መግባባት ላይ ተደርሶና በግማሽ ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ ተደርጎ የመልካም አስተዳደር ዕቅድ በመከለስ ወደ ተግባር በማባቱ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ባይሆንም በዘርፉ በየአካባቢው በተጠናከረና በተደራጀ አካኋን ድጋፍና ክትትል ማድረግ በመቻሉ የተሻለ ጅምር ይታያል፡፡

### 2.1 ከመልካም አስተዳደር አንፃር በዘርፉ ተዋናዮች እስከ አሁን ለተነሱ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾችን በተመለከተ፡ -

- **የሚልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን** መፍታት ይቻል ዘንድ ዘርፉ በፈጠረው ቅንጅታዊ በመሳሪያ አቅርቦት፣ በክላስተር ሜከላት እንዲሁም ከሀይል አቅርቦት ጋር የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ይቻል ዘንድ የየተቋሙ ኃላፊዎች በየ 15 ቀኑ እየተገናኙ በመወያየትና የተገኙ ዉጤቶችን በማምገም ላይ ያሉ ሲሆን በዚህም አበረታች ዉጤቶች እየተመዘገቡ ነዉ፡፡ ለአብነት ከኃይል አቅርቦት ጋር ያሉ ችግሮች እየተፈቱ ሲሆን፣ ከመሳሪያ አቅርቦትም ጋር ተያይዞ በደቡብ ካፒታልና በኢትዮጵያ ልማት ባንክ በኩል ማሽነሪዎች እየቀረቡ ተከላዎችም በመካሄድ ላይ ናቸዉ በተጨማርም የክላስተር ብሎኮችን የዉስጥ ኤሌክትሪክ ኢንስታለሽን ችግሮች መፍታት እንዲቻል የኢንደስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፓረሽን እንደአዲስ የኢንስታለሽን ስራዎችን በሁሉም የክላስተር ሜከላት እያከናወነ ሲሆን ከዚህም ጎን ለጎን የአጥር፣ የሽንት ቤት እንዲሁም የደረጃ ማሻሻል ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ ከቴ/ሙ/ተቋማት ጋር በተመሳሳይ ሚልኩ ያሉትን ችግሮች መፍታት ይቻል ዘንድ በቢሮ ደረጃ ወይይቶች የተከናወነ ሲሆን በተቀማጡ አቅጣጫዎች መነሻ ችግሮች የሚፈቱ ይሆናል፡፡
- **የሊዝ ማሽንን በወቅቱ ለኢንዱስትሪያሊስቶች ማቅረብን በተመለከተ**

  ከማኑፋክቸሪንግ ኢንደስትሪ ዘርፍ፣ ከደ/ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ እና ከብረታብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የተወጣጡ የባለሙያዎች ቡድን በሥራው ላይ እንዲሰማራ በማድረግ ቀጥሎ በቀረበው ዝርዝር ማስረት ችግሩን ለማቃለል ተችሏል፡፡ ለአብነትም አስቀድሞ ማሽነሪ የቀረበላቸው ሆኖም ተተክለወና ተገጥመው ወደ ሥራ ያልገቡትን ከተሞች ይነሳ የነበረው ቅሬታ የተከላወና የገጠማው ሥራ በአሁኑ ሰዓት የመበራት ችግር ካለባቸዉ መዋቅሮች ዉጪ ተጠናቋል፡፡ በወልቂጤ፣ ቡታጅራ፣ ወራቤ፣ ሀላባ፣ ሀዋሳ፣ ዲላ፣ ወላይታ ሶዶ ( በክላስተር ሜከላት ያሉ)ና አርባምንጭ ከተሞች የተከላ፣ የኮሚሽኒንግና ሥልጠና ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን የሀይል አቅርቦት ችግር በመኖሩ ምክንያት የኮሚሽኒንግ ሥራ ቢሰራም ወደ ሥራ ያልገቡ ከተሞች አርባ ምንጭ (ብረታብረት ማሽን)፣ ተርጫ ጂንካ፣ አረካ፣ ቦዲት፣ ይርጋጨፌ፣ ማሻ፣ ሚዛን አማን፣ ሳወላ፣ ሆሳዕና፣ አለታ ወንዶና ወላይታ ሶዶ (በግል ሥራ ሜከላት የተተከሉ) ከተሞች እስካሁን ወደሥራ ሊገቡ አልቻሉም፡፡

  በተጨማርም ማሽን በተተከለባቸዉና ስልጠና በተሰጠባቸዉ ቦታዎች ሲነሳ የነበረው የማሽን ርክክብ ማዘግየትን ለመቅረፍ ከደቡብ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ/ማ እና ከማኑፋክቸርንግ ዘርፍ ባለሙያዎችን በመቀናጀት ለኢንደስትሪዎቹ የመበራት ችግር ካሉባቸዉ መዋቅሮች ዉጪ ርክክብ ተፈጽሟል፡፡

  በፍሌክሰብል ዎርክሾፖችም ሲነሳ የነበረዉ የርክክብ ጥያቄ ከደቡብ ካፒታል ዕቃዎች ፋይናንስ አቅራቢ አ/ማነበርና ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ባለሙያዎችንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት ማሽነሪዎችን ከክልሉ ንግድ ኢንዱስትሪ ቢሮ ለደቡብ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ/ማነበር በማስተላለፍ በተመሳሳይ የደቡብ ካፒታል ዕቃ ፋይናንስ አቅራቢ አ/ማ ለፍሌክሴብል ወርክሾፖች ሂደቱን ጠብቆ እንዲያስተላልፍ በሚደረጉ ምላሽ አግኝቷል፡፡

**በዘርፉ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የኃይል አቅርቦት ችግር**

ከሀይል አቅርቦት ጋር በተያያዘ ችግሩን ለመፍታት ከከተማ እስከ ሪጅን ብሎም እስከ ፌደራል የሚመለከታቸው አካላት ድረስ በተደረጉ ወይይቶችና የሥራ ግንኙነቶችና ትግል መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም በተለይም ከዘርፉ ተዋናዮች ወቅታዊ የኃይል ፍላጎትና አንገብጋቢነት አንፃር ችግሩ አሁንም የሚመለከታቸዉን አካላት ጠንካራና የተደራጀ ቅንጅት የሚፈልግ መሆኑ ግድ የሚል ቢሆንም በእስካሁኑ ርብርብ፤

**የትራንስፎርመር አቅርቦትን በተመለከተ፡-** ከይርጋጨፌ፣ ተርጫ እና ሳዉላ ከተሞች በስተቀር በሁሉም ችግሩ በነበረባቸዉ ከተሞች ትራንስፎርመር ቀርቦ ተከላ ተከናዉኗል፣ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ በዋናነት ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅራቢ ተቋማት እና ከሚመለከታቸው አካላት አኳያ መከናወን ያለባቸው ተግባራት በትኩረት ባለመከናወናቸው ምክንያት ወደ ስራ አልተገባም፡፡ በዚሁ መሰረት ተርጫ እና ጂንካ ከተሞች ላይ ዛሬም ድረስ ይህ ክፍተት የሚልካም አስተዳደር ችግር እየሆነ ነው፡፡ ከእነዚህ ወስጥ የሳዉላ ከተማ ችግር የተፈጠረዉ ከከተማ አስተዳደሩ የሚጠበቀዉን ክፍያ በወቅቱ ባለሟጸሙ ምክንያት ማህበራት ለእንግልት ተዳርገዋል፣ በይርጋጨፌ ከተማም የኮምፓክት ትራንስፎርመር በሀገር ወስጥ ባለመኖሩ ምክንያት በክላስተር ሜከሉ የተገጠሙ ማሽነሪዎች ሥራ መጀመር አልቻሉም፡፡

**የቆጣሪ አቅርቦትን በተመለከተ፡-** ችግሩን ካነሱት ከተሞች ወስጥ ሚሻ፣ ቴፒ፣ ወልቂጤ፣ ቡታጅራ፣ ወራቤ፣ ሆሳዕና፣ አርባ-ምንጭ ሀላባ፤ አለታወንዶና ዲላ ከተሞች ምላሽ አግኝተዋል፡፡

ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ችግር በዘለለ በሁሉም ከተሞች በሚገኙ የማምረቻ ክላስተር ሜከላት ወስጥ በየብሎኮቹ የወስጥ ለወስጥ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ችግር ያለባቸዉ በመሆኑና የመስመሮቹ የኤሌክትሪክ መሸከም አቅም እንዲሁም የተቀጠሉት ሶኬቶች ሲንግል ፌዝ በመሆናቸው ምክንያት የማሽነሪዎች ተከላ ቢካሄድም ማሽነሪዎቹን ለስልጠና ማንቀሳቀስ ባለመቻሉ ስልጠናዎችም በሚፈለገዉ አግባብና በተያዘለት ጊዜ ያልተሰጡ ሲሆን ለኢንደስትሪያሊስቶችም በአሁኑ ወቅት ለስራቸዉ ችግር የሚፈጥር በመሆኑ በአሁን ወቅት በሁሉም ከተሞች የክላስተር ሜከላት የችግሮች ልየታ ተሰርቶ ለችግሮቹ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል ከየከተማው የቀረበና በቀጣይ የሚቀርቡ ማሽነሪዎችን በሚመጥን መልኩ የጥገናና፣ እድሳትስና የኤሌክትሪክ ኢንስታሌሽን እንዲሁም የመጸዳጃ ቤትና የዘርያ አጥር ግንባ (ታንዳርዳይዝድ) የሚድረግ ሥራ በመጀመሩ በቅርቡ ሙሉ በሙሉ መፍትሔ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

**የገበያ ድጋፍ ፍትሀዊነትን በተመለከተ፣**

የኢንደስትሪያሊስቶች የገበያ ችግር ለመቅረፍ የገበያ ማጠረታቻ ደንቡ ለማሻሻል እየተሰራ ያለ ቢሆንም ከዚህ በፊት በክልሉ መንግሥት የጸደቀዉን የገበያ ማጠረታቻ ደንብ ተግባራዊ ከሚድረግ ጋር በተያያዘ አሁንም ሰፊ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ በአንዳንድ መዋቅሮቻችን ችግሩን በትግል ለመፍታት እየተሞከረ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ካፋና ደ/አሞ መዋቅር ባደረጉት ትግል ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የገበያ ድገፍ እንዲያገኙና የማጠረታቻ ደንቡ ተግባራዊ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ወቅቱን ያገናዘበ የገበያ

ማበረታቻ የህግ ማቀፍ/ ደንብ ረቂቅ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በማስጸደቅ ወደ ሥራ ለማስገባት ዝግጅት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

## 3. የኪራይ ሰብሳብሳቢነት ምንጮችን ከማድረቅ አንፃር

### 3.1 በአማካከት ግንባታ የተሰራ ስራ

- በዘርፉ የሚስተዋሉ የኪራይ ምንጮች ምን እንደሆኑ በማየት እንዴት በትግልና በአሰራር ማዝጋት እንዳለባቸው በየደረጃው ከሚገኘው የዘርፉ አሜራርና ፈጻሚ ጋር በተፈጠሩ መድረኮች መግባባት ላይ በመድረሱ በየአደረጃጀቱ የሚገባ አጀንዳ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በተለይም አምራቾቹ በጥራት፣ በጊዜና በዋጋ ተወዳዳሪ መሆን ብቻ አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑ በተለያዩ መድረኮች ዋና አጀንዳ ሆኖ ትግል ተደርጎበታል፡፡
- ማንግስት ኢንዱስትሪያሊስቶችን ለማበረታታት ያወጣውን የገበያ ማበረታቻ ከታለመለት አላማ ወጪ በሚያወሉ ተቋማት በየአካባቢ ተገቢው ትግል ማድረግ ተጀምሯል፡፡ በዚህ ረገድ የካፋ፣ የደቡብ ኦሞ፣ የጉራጌ፣ የወላይታ ፣ ጋሞ ጎፋ ዞኖች ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- የሂሳብ ዝርጋታና የኦዲት ስራዎች በኢንደስትሪያሊስቶቹ በኩል እንዲያድግ እየተደረገ ያለዉ ጥረት የሚያበረታታ ቢሆንም በማስኩ በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል በተለይም ኦዲተር በታችኛው መዋቅር በበቂ ሁኔታ ያለመኖሩ፣ በሂሳብ አሰራርና አማዘጋገብ ላይ ኢንዱስትሪያሊስቶቹ ያላቸው ግንዛቤ ወስን መሆን እንደማነቆ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፣

### 3.2 የአሰራር ስርዓት በማዝርጋት የተሰራ ስራ

- የኪራይ ምንጭን ከማድረቅ አንጻር በሴክተሩ የሚፈጸሙ ማናቸውንም ተግባራት በተቀማጠው አሰራር ማስረት በልማት ሰራዊት አደረጃጀቶችና በግንባር ቀደሞች እየተመራ ብቻና በግልጽነት እንዲፈጸሙ የቢሮው የግንባር ቀደም አደረጃጀቶች የለውጥ ፕሮግራሙን በጥብቅ ዲሲፕሊን እንዲመሩት እየተደረገ ይገኛል፡፡
- በክልል መዋቅር በኩል የለውጥ ስራዎች በተጠናከረ አግባብ በተቀማጠዉ የአሰራር ስርዓት ማስረት ለማስራት ከመቼውም ግዜ በበለጠ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

## 4 በአማካከትና በተግባር የተጋለጡ የኪራይ ሰብሳቢነት የተወሰደ ተጨባጭ እርምጃ እና የተገኘ ውጤት

- በደቡብ ኦሞ ዞን ጂንካ ከተማ ለበርካታ ጊዜያት በጥቂት ማህበራት እጅ የነበረው ከሆስፒታል አወትሶርስ የተደረገው ገበያ በተገቢው ከተገማመ በኋላ የማህበሩ ቁመና ጎስት መሆኑ በሚጋገጡ እንዲፈርስ ተደርጎ በአዲስ መልክ ለአዲስ ማህበራት ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ገበያው በጨረታ እንዲተላለፍ መደረጉ
- በፋይናንስ ማስሪያ ቤቶች ዙሪያ ያለ የግንዛቤ ክፍተት ካለመሟላት የሚመጣጭ ችግር በተጨማሪ በኪራይ ሰብሳቢነት አማካከትና ተግባር ጋር በተያያዘ የሚፈጠር ችግር የተለያዩ መድረኮች

በመፍጠር በገበያ ድጋፍ ተግዳሮት የሚፈጥሩ አካቢያዎች ተለይቶ ግምገማ በማድረግ በተቀማጠዉ አቅጣጫ መሰረት አሁን በወሰን ደረጃም ቢሆን ችግር መቅረፍ መቻሉ፤

**ክፍል ሁለት**

**2.1 የማስፈጸሚአቅምግንባታሥራዎች**

1. የሁለተኛውን ዙር የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻና የ2008 በጀት ዓመት አፈጻፀም መሰረት ያደረገ የስራ ሂደቱ ብቁ ዕቅድ በማዘጋጀት ተገቢው ኦረንቴሽን እና ግልፅ ተልዕኮ በመስጠት ፈጻሚ ለማዘጋጀት በእቅድ በተያዘው መሰረት ከክልል እስከታችኛው መዋቅር በየደረጃው የግብ ስምምነቶችን መነሻ ያደረገና የወጡት ተኮር ዕቅድ በማዘጋጀትና በሚፈራረም ወደተግባር የተገባ ሲሆን የመጀመሪያ መነፈቅ አመት የሥራ አፈጻጸም ግምገማ በማድረግና የቀጣይ ወራት እቅድ ክለሳ በማድረግ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡
2. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ቆጠራ ወቅት የተገኙ ኢንዱስትሪዎችን አዳዲስ አደረጃጀቶችን በመፍጠርና የተፈጠሩ አደረጃጀቶች በማጠናከር የስራሂደቱን 41 ግቦች በተደራጀ የልማትሰራዊት በ19ኙም መዋቅሮች በየሩብዓመቱ 100% ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በአማካይ ከተጣሉ ግቦች 70% ለማከናወን ተችሏል፡፡
3. በታችኛዉ መዋቅር በኩል በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ 269 አመራሮችና **858** ባለሙያዎች በድምሩ ለ 1127 ተሳታፊዎች በተለያዩ ርእሶች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት በእቅድ ተይዞ ለ**358** አመራሮች እና **1550** በድምሩ **1908** ፈጻሚዎች ስልጠና በመስጠት ከ 100 % በላይ ማከናወን ተችሏል፡፡
4. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ **400** በብረታ ብረትና እንጨት፣ **120** በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ **160** በጨርቃጨርቅና አልባሳት እና **80** በቆዳና ቆዳ ውጤቶች በድምሩ ለ **760** አንቀሳቃሾች የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት በእቅድ በተያዘው መሰረት 371 በብረታ ብረትና እንጨት፣ **180** በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ **145** በጨርቃጨርቅና አልባሳት እና **80** በቆዳና ቆዳ ውጤቶች በድምሩ ለ 759 አንቀሳቃሾች የክህሎት መሻሻ ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ**99** በመቶ ይሆናል፡፡

**በጉድለት፡**

- በክልል በኩል በካፒታል በጀት ተይዞ ሊሰጥ ታቅዶ የነበረው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ አንቀሳቃሾች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች አስከአሁን አለሚጸማቸዉ፡፡
- ሪፖርት በወቅቱና በሪፖርት ፎርማት መሰረት ከየመዋቅሩ ከማቅረብ አንጻር ሰፊ ክፍተቶች መኖራቸው በተለይ ጌደኦ፣ ሸካ ዞኖችና ባስኬቶና ኮንታ ልዩ ወረዳዎች ሪፖርት በወቅቱ እየላኩ ያለማሆኑ፤

- ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪያሊስቶች በቁጠባቸው ማስረት በተለያዩ ምክንያቾች ወቅቱን የጠበቀ የማሽነሪ አቅርቦት ያለማኖሩ

## ክፍል ሶስት

## የ2009 በጀት አመት የልማት ሥራዎች የዘጠኝ ወር እቅድ አፈጻጸም

1) የአንቀሳቃሾችን አቅም ለማጎልበትና ያለባቸዉን የክህሎት ክፍተት ለመሙላት ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር በመቀናጀት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩና ለሚሰማሩ ለ 31,923 ወንደችና ለ 29,550 ሴቶች በድምሩ ለ 61,473 አንቀሳቃሾችና 7,795 ጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክቴንሽን ድጋፍ ለማስጠት ታቅዶ ለ 6,879 ወንድ ለ 3,070 ሴት በድምሩ ለ 9,949 አንቀሳቃሾችና ለ2,870 ጥቃቅን፣አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክቴንሽን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በተቋማት 36.8% እና በአንቀሳቃሽ 16.2% ይሆናል፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ከምባታ ጠምባሮ ዞን፣ሲዳማ፣ወላይታ፣ ጋ/ጎፋ ዞኖችና ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ሲሆኑ ፣ አጥጋቢ አፈጻጸም ያላቸው ደግሞ ጉራጌ፣ሀድያ፣ኮንታ፣ሃለባ፣ ስልጤ፣ ካፋ፣ ደ/ኦሞ ሲሆኑ ቀሪዎቹ መዋቅሮች ማለትም ፣ሰገን ህዝቦች፣ባስኬቶ፣ዳወሮ፣የም፣ቤንች ማጂ ዞን ዝቅተኛ አፈጻጸም ያሳዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም የዚህ ግብ አፈጻጸም ከዕቅድ በላይ የተከናወነ ሲሆን በየደረጃው የግንዛቤ ማስደግ ሥራው በተሻለ ሁኔታ በማካሳኑና የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በተሻለ ሜኩ ድጋፍ እየሰጡ በመሆኑ ነው፡፡
2) ለ27,428 ወንደችና ለ 26,849 ሴቶች በድምሩ 54,277 አንቀሳቃሾችን እስከ ደረጃ 4 በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን በማብቃት 6,836 ተቋማት ምዘና እንዲደረግላቸው ለማድረግ ታቅዶ ለ 6,879 ወንድ ለ 3,070 ሴት በድምሩ ለ 9,949 አንቀሳቃሾችና በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን በማብቃት ለ2,870 ተቋማት ምዘና ሜድረግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙ በአንቀሳቃሽ 18.3 %ና በተቋም 42 በመቶ በማሆን ተከናወኗል፡፡ በተጠቃሚ ቁጥር ሲታይ ምንም ያላከናወኑ መዋቅሮች ዳዎሮ፣ ቤ/ማጂ ዞኖችና የሜና ኮንታ ልዩ ወረዳዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ መዋቅሮች ዝቅተኛ አፈጻጸም የተመዘገበባቸው ናቸው፡፡
3) ምዘና ከተደረገላቸው አንቀሳቃሾች ወስጥ 80%ቱ ማለትም 21,728 ወንድ 21,475 ሴት በድምሩ 43,202 አንቀሳቃሾች እና 5416 ተቋማት ለማብቃት ታቅዶ 2346 ወንድ 694 ሴት በድምሩ 3040 አንቀሳቃሾች እና 946 ተቋማት ማብቃት የተቻላ ሲሆን አፈጻጸሙ በአንቀሳቃሽ 7% እና በተቋም 17.5 በመቶ በማሆን ተከናወኗል ፡፡ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ከምባታ ጠምባሮ ዞኖችና ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ሲሆን ሌሎች መዋቅሮች ከዕቅድ በታች ያከናወኑ ናቸው፡፡

   **ግብ 2ና ግብ 3** አፈጻጸማቸው ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የታችኛው መዋቅሮቻችን ከቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር በቅንጅት ከማስራት አንጻር ጉድለቶች በመኖራቸው አፈጻጸሙ ዝቅ እንዲል አድርጎታል፡፡
4) በቴ/ሙያ ተቋማትና በጥቃቅንና አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ዝግጁ የሆኑና የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚኪሄድባቸው በብረታብረትና እንጨት 13፣ በአግሮፕሮሰሲንግ 9፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት 3፣ በቆዳ ስራ 3 በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ 3 በድምሩ 32 ፕሮቶታይፖች ለማዘጋጀት በእድቅ በተያዘው ማስረት በብረታብረትና እንጨት 47፣ በአግሮፕሮሰሲንግ 1፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት 3፣ በቆዳ ስራ 4 እና በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ 0 በድምሩ 55 ፕሮቶታይፖች ተማርተው የተሸጋገሩ ሲሆን አፈጻጸሙ 156% በማሆን ተከናወናል ፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገበት ከፋ፣ሃድያ፣ ስልጤ፣ ወላይታ፣ ከምባታ

ጠማሮ፣ ጋሞጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጉራጌ ዞኖችና ሃዋሳ ከተማና ሃላባ ልዩ ወረዳ ሲሆኑ ሌሎች መዋቅሮች ዝቅተኛ አፈጻጸም አስመዝግበዋል፡፡

- በአብነር ተቋም በብረታብረትና እንጨት 102፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ 66፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት 32፣በቆዳ ስራ 32፣ በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ 23፣በድምሩ 256 ታቅዶ በብረታብረትና እንጨት **152**፣ በአግሮ ፕሮሰሲንግ **0**፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት **17**፣ በቆዳ ስራ **19**፣ በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ **0**፣ በድምሩ **188** አብነር ተቋማት የተፈጠሩ ሲሆን አፈጻጸሙ **73**% በመሆን ተከናወኗል፡፡
- ከተጠቃሚ አንጻር በብረታብረትና እንጨት 998፣በአግሮ ፕሮሰሲንግ 624፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት 325፣ በቆዳ ስራ እና 325፣ በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ 225 በድምሩ 2496 አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በእቅድ በተያዘው ማእረት በብረታብረትና እንጨት 824፣በአግሮ ፕሮሰሲንግ **0**፣በጨርቃጨርቅና አልባሳት **166**፣ በቆዳ ስራ **95** እና በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ **0** በድምሩ **1085** አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ ሲሆኑ አፈጻጸሙ **43**% በመሆን ተከናወኗል፡፡
- በሁሉም የስራ ማስኮች ብር 2,964,897 ሃብት ለመፍጠር ታቅዶ ብር **6,662,000** ሀብት መፍጠር ተችላል አፈጻጸሙ **224**% በመሆን ተከናወናል፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስማዝገቡ ደ/ኦሞ፣ሀድያ፣ወላይታ፣ሲዳማ ዞኖችና ሀዋሳ ከተማ ሲሆኑ አጥጋቢ ወጤት ያስመዝገቡ ካፋ፣ ጋ/ጎፋና፣ ጉራጌ ዞኖችና ሀላባ ልዩ ወረዳ ሲሆን ዳወሮ፣ ቤ/ማጂ፣ሸካ፣ ሰገን ዞኖችና ባስኬቶ፣ ኮንታና የም ልዩ ወረዳዎች ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዝገቡ መዋቅሮቻችን ናቸው፡፡
- ከፍተኛ አፈጻጸም የተመዝገበበት ምክንያት ኢንዱስትሪያሊስቶቻችን አዳዲስ ቴክሎጂዎችን ለመቀረጅና ለማሻሻል የተሻለ ተነሳሽነት በማሳየታቸው ሲሆን በተለይ በደ/ኦሞ ዞን ጂንካ ከተማ ባስልኤል የተሰኘ የብረታብረት ሥራ ኢንተርፕራይዝ የተለያዩ ማሽነሪዎችን ፈትቶ በማየትና በመቀረጅ እንዲሁም አሻሽሎ በማስራት ወጠቃማ ተግባር በማከናወኑ አፈጻጸሙ ከፍ ለል ችሏል፡፡ ይሁንና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪያሊስቶቻችን አንዳንድ ቴክኖሎጂዎችን በቀጥታ በመቀረጅና በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ማማሀራን ሳይቃኑ የሚያበዘብት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ ነገር ግን የሚቀረጹና የሚሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች በአብዛኛው በእንጨትና ብረታብረት ቴክኖሎጂዎች ላይ የታጠሩ ሲሆኑ በአግሮፕሮሰሲንግ ዘርፍም ወስን እንቅስቃሴዎች ይታያሉ፡፡ ይሁንና በቆዳና ቆዳ ወጤትና በጨርቃጨርቅና አልባሳት ዘርፍ የሚታየው አፈጻጸም እጅግ ዝቅተኛ ሲሆን ለዚህም በክልላችን ከሚገኙ ቴ/ሙ/ተቋማት በዘርፉ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ተቋማት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው መሆኑ የዘርፉን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዝቅተኛ እንዲሆን አስችሎታል፡፡
- በተጨጭም ኢንዱስትሪዎቻችን አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በራሳቸው ተነሳሽነትና ፈጠራ በማምረት ላይ ቢሆኑም በቴክኒክና ሙያ ማማሀራንና ተቋማት በዝርዝር ስፔሲፊኬሽን ዝግጅትና ዲዛይኒንግ እየተደገፉ ያለመሆናቸው ለሚያመርቱት ማሽነሪዎች ቀጣይነት፣ አዋጭነትና የተሻለ ተጠቃሚነትን ከሚጋገጥ አንጻር ጉደለቶች የሚተዋለበት ነው፡፡ ለአብነትም የተመረቱ ፕሮቶታይፖች፡- የአካል ጉዳተኞች ማቀሳቀሻ ሞተር ሳይክል፣ የአካል ጉዳተኞች ማዳጃና ንቀሳቃሽ የሆስፒታል አልጋ ከነ ግሉኮስ ማቀያው፣ የቡና መፍጫ ወፍጮ የሸንከርት መፍጫ የፈሳሽ ሳሙና ማምረቻ፣ የእንጨት ማስንጠቂያ፣ የብሎኬት ማምረቻ...

5) 211 የማርያ ሊዝ ተጠቃሚ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የማሪያወን ዋጋ 15% ብር 32,638,205 እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ በቁጥር **269** ተጠቃሚዎች **61,357,224**ብር እንዲቆጥቡ ማድረግ የተቻለ ሲሆን

አፈጻጸሙም ከተቋም አንጻር 358% ሲሆን ከብር አንጻር 127 በመቶ በመሆን ተከናዉኗል፡፡ በተቋም ብዛት ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡት ሃድያ፣ ጉራጌ፣ ከፋ፣ ሲዳማ፣ ዳወሮ፣ ጋሞጎፋ፣ ሰገንና እና ከምባታ ጠምባሮ ዞኖች፣ ሃዋሳ ከተማ፣ የም፣ ሃላባና ባስኬቶ ልዩ ወረዳ ሲሆኑ በተቆጠበ ገንዘብ በጣም ከፍተኛ አፈጻጸ ያስመዘገቡ ጉራጌ፣ ስልጢ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ሃድያ፣ ቤንች ማጂ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ዳወሮ፣ ሲዳማ፣ ጌዴኦ፣ እና ሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞኖች እና የምና ባስኬቶ ልዩ ወረዳ ሲሆኑ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ሲሆን አጥጋቢ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ደግሞ ከፋና ጋሞጎፋ ዞኖች ናቸው፡፡ ወላይታ ፣ሸካ ዞንና ሃዋሳ ከተማና ሃላባ ልዩ ወረዳ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸው ሲሆን ኮንታ ልዩ ወረዳ ምንም ያላከናወነ መሆኑ ነው፡፡ ለአፈጻጸሙ ከፍ ማለት የቁጠባ ሞቢላይዜሽንና የሊዝ ማሽን ፍላጎት ፈጠራ ሥራ በትኩረት በመከናወኑና በወሰን ሜልኩም ቢሆን የቀረቡ ማሽነሪዎች ወደ ተግባር መግባታቸው በፈጠረው መነቃቃት የግቡ አፈጻጸም ከፍ እንዲል አስችሎታል፡፡ በተለይም በልማት ባንክ በኩል ለጸደቁ የሥራ ዕቅዶች 20 % የሥራ ማስኬጃ በአይነትና በጥሬ ገንዘብ ከባንክ በተረጋገጠ ሰነድ የቀረበ የቁጠባ ማጠን ሲሆን በየመዋቅሩ የማሽነሪ ሊዝ ተጠቃሚ ለመሆን በኦሞ ሚይክሮ ፋይናንስ ተቋም በኩል የተቆጠበ ገንዘብ መኖሩን የመዋቅሮች ሪፖርት ያመላክታል፡፡

6) ለ210 የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 458 ድጋፍ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙም 218 % በመሆን ተከናዉኗል፡፡ በቢዝነስ ፕላን ዝግጅት ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡት ወላይታ፣ደቡብ ኦሞ፤ጋሞ ጎፋ፤መሀላባ፤ሲዳማ እና ከ/ጠምባሮ ዞኖች፣የም እና ሃዋሳ ከተማ ሲሆኑ መካከለኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ስልጤ ዞን፤ ባስኬቶ እና የም ልዩ ወረዳዎች ናቸው፡ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያሳዩ ሃድያ፣ዳወሮ፤ሰገን፤ቤንች ማጅ፤ጉራጌ፤ እና ከፋ ሲሆኑ ምንም ያላከናወኑት ሸካ ዞን እና ኮንታ ልዩ ወረዳ ናቸው፡ ከፍተኛ አፈጻጸም የተመዘገበበት ምክንያት በግለሰብ ደረጃም ጭምር የቢዝነስ ፕላን እያሰሩ ወደ ሥራ የመግባት ልምድ እየዳበረ በመምጣቱ ሲሆን በቀጣይም በዘርፉ የተዘጋጁ ቢዝነስ ፕላኖች ወደ መካሪያ ሊዝ አቅራቢ ተቋማት ቀርበው ወደ ተግባር እንዲገቡ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማደረግ ይኖርበታል፡፡

7) በክልላችን በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሥራ ማስክ የተሰማሩና የሚሰማሩ ኢንዱስትሪያሊስቶችን የማሽነሪ ሊዝ ተጠቃሚዎች ለማድረግ ብር 192,342,858.00 የመካሪያ ሊዝ ብድር ለማመቻቸት በእቅድ በተያዘው መሰረት በደቡብ ካፒታል ዕቃዎች አቅራቢ አ/ማ ብር 25,322,501 የሚገመት የብድር ጥያቄ የያዘ 186 የንግድ ሥራ ዕቅድ ቀርቦ ፀድቆ የማሽነሪ ግዥ ሂደት ላይ ሲሆን አጠቃላይ ከታዘዙት ማሽነሪዎች መካከል 159 ማሽነሪዎች ተገዝተው የቀረበ ሲሆን ቀሪዎቹ ማሽነሪዎች በአቅራቢ ደርጅቶች በመቅረብ ሂደት ላይ ናቸው፡፡ በሌላ ሜልኩ ለኢትዮጵያ ልማት ባንክ የብር 1,702,909,913.16 ብር የብድር ጥያቄ የያዘ 272 የንግድ ሥራ ዕቅድ የቀረበ ሲሆን ከዚህም ወስጥ የብር 516,669,598.35 ብር ብድር የያዘ 83 የንግድ ሥራ ዕቅድ ጸድቋል፡፡ ቀሪዎቹ 189 የንግድ ሥራ ዕቅዶች በተለያየ ሜልኩ የማጣራትና አስፈላጊ መስፈርቶችን በማሟላት ሂደት ላይ የሚገኙ ሲሆን እስከአሁን አራት ማሽነሪ የቀረበ ሲሆን ቀሪዎቹ በጨረታ ሂደት እና ለግዥ የቀረቡት በአቅራቢ ድርጅቶች በመቅረብ ሂደት ላይ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በደቡብ ካፒታል እቃዎች ፋይናንስ ንግድ ስራ አክሲዮን ማህበርና በኢትዮጲያ ልማት ባንክ በድምሩ ብር 541,992,099 የመካሪያ ሊዝ ብድር ተመቻችቷል፡፡ አፈጻጸሙም ከ 100 % በላይ ነው፡፡ አፈጻጸሙ ከፍ ያለበት ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት ሰፊ የንቅናቄ መድረኮችን በማመቻቸት ሃስቱን የልማት አቅሞች አቀናጅቶ መምራት በመቻሉ ነው፡፡

8) በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ ወጣቶችና ሴቶች ቅድሚያ በመስጠት የማምረቻ መካሪያ ሊዝ ተጠቃሚ ለማድረግ 80 የብረታብረት፣ 48 በእንጨት፣27 በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ 20 በጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ 12 በቆዳ ስራ

8 በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ በድምሩ **196** ተቋማትን ተቃዶ 98 የብረታብረት፣ 89 በእንጨት፣ **8** በአግሮ ፕሮሰሲንግ፣ 32 በጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ 4 በቆዳ ስራ፣ 7 በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ በድምሩ **238** ተቋማት በማርያ ሊዝ ተጠቃሚ እንዲሁኑ ተመቻችቷል አፈጻጸሙ በመቶኛ 121% ነው፡፡ የተመቻቹ ሁኔታዎች በዝርዝር ሲታዩ የቁጠባ፣ የቢዝነስ ፕላን ዝግጅትና ከማሪያ አቅራቢ ተቋማት ጋረው የወል ስምምነት የሚፈጸም ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ለ108 ተቋማት የማሽነሪ አቅርቦትና ተከላ በመከናወን ላይ የሚገኝ ሲሆን ለ52 ተቋማት የማሽነሪ ተከላ ተከናወኗል፡፡

9) በአንቀሳቃሽ 657 በብረታብረት፣ 372 በእንጨት፣228 በአግሮፕሮሰሲንግ፣ 186 በጨርቃጨርቅና አልባሳት፣ 146 በቆዳ ስራ 85 በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ በድምሩ 1,672 አንቀሳቃሾችን በማርያ ሊዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ 356 በብረታብረት፣ 430 በእንጨት፣ 40 በአግሮፕሮሰሲንግ፣213 በጨርቃጨርቅና አልባሳት ፣20 በቆዳ ስራ 36 በኮንስትራክሽን ግብአቶች ማምረቻ በድምሩ **1095** አንቀሳቃሾችን በማርያ ሊዝ ተጠቃሚ ሆነዋል አፈጻጸሙ **65.5** % በመሆን ተከናወናል፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገበ መዋቅር ሲዳማ ሲሆን አጥጋቢ አፈፃፀም ያስመዘገበው ስልጤ ዞን ሲሆን ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ዳወሮ እና ጋሞ ጎፋ ዞን ሲሆኑ ቀሪዎቹ መዋቅሮች ምንም ያላከናወኑ ናቸው፡፡

10) ለማርያ ሊዝ የዋለውን ብር 27,258,288 ብድር ለማስመለስ በእቅድ ተይዞ ብር **552892.01** ማስመለስ የተቻላ ሲሆን አፈጻጸሙ **2** % በመሆን ተከናወኗል፡፡ ሀዋሳ ከተማ እና ከምባታ ጠምባሮ፣ ሀላባ፣ ዲላና ሶዶ ከተሞች መዋቅሮች ብድር የማስመለስ ሂደቱን ያከናወኑ ሲሆን በአጠቃላይ ለአመላለሱ ዝቅተኛ መሆን የማሽነሪ ሊዝ ሥርዓቱ ገና በስርጭት ሂደት ላይ መሆኑ፡፡

11) በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኙና አዲስ ወደ ሥራ የገቡ 1858 ጥቃን፣ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሂሳብ ዝርጋታ ለማካሄድ በእቅድ ተይዞ 3435 በማከናወን አፈጻጸሙ ከ 185% በመሆን ተከናወኗል፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡት ጉራጌ፣ ሃድያ፣ ቤንችማጂ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ጋሞጎፋ፣ ደቡብኦሞ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ዳወሮና ሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞኖች፣ ሃዋሳ ከተማና የም እና ባስኬቶ ልዩ ወረዳዎች ሲሆኑ፣ አጥጋቢ አፈጻጸም ያስመዘገበው ደግሞ ስልጤ ዞን ነው፡፡ ለአፈጻጸሙ ከፍ ማለት ምክንያቱ በሚደረግላቸው ድጋፋዊ ክትትል ምክንያትየማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተቋማት የሂሳብ ዝርጋታ፣ አያያዝና ምዝገባ ግንዛቤ ከመጨመሩም በላይ ከዚህ ቀደም በማነበር የተደራጁ ማነበራት ብቻ ሂሳብ የሚዘረጋላቸው ሲሆን በአሁኑ ወቅት በግልም ጭምር የማኑፋክቸሪን ኢንዱስትሪወን ዘርፍ ሲቀላቀሉ የሂሳብ ዝርጋታ የሚሰራላቸው በመሆኑ አፈጻጸሙ ሊጨምር ችሏል፡፡

12) በቁጥር የ1654 ነባር ጥቃቅን አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ሂሳባቸው ምርመራ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ የ2234 ተቋማት ሂሳባቸው ተመርምሯል አፈጻጸሙ 135%ነው፡፡ በጣም ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡት ወላይታ፣ ሲዳማና ከ/ጠምባሮዞኖች እና የም ልዩ ወረዳ ሲሆኑ ጋ/ጎፋ፤ዳወሮ እና ጉራጌ ዞኖች መካከለኛ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሲሆን፣ሀድያ፤ከፋ እና ቤንች ማጅ ዞኖች እና ሀላባ ልዩ ወረዳ አጥጋቢ አፈፃፀም አስመዝግቧል፤ደ/ኦሞ፤ሰገን ዞኖችና ባስኬቶ ልዩ ወረዳ ዝቅተኛ አፈፃፀም ሲያስመዝግቡ ከፋ፤ሸካ እና ስልጤ ዞኖች ምንም ያላከናወኑ ናቸው፡፡

13) በ9 ወሩ 19ኙም መዋቅሮች በክልሉ ወስጥ በሚገኙ ከተሞችና ወረዳዎች በሰባቱም የማንፋክቸሪነግ የስራ ማስኮች የዘርፍ ማህበራት እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች የአደረጃጀት ድጋፍ 3ዙር ለመደገፍ በእቅድ በተያዘው መሰረት 3 ዙር ድጋፍና ክትትል በማድረግ 100% ተከናወኗል፡፡ ይሁንና አዳዲስ የዘርፍ ማነበራትንና የዘርፍ ማነበራት ምክርቤት ለማቋቋም እቅዱ ገና በሁለተኛው ሩብ ዓመት ወደ ሥራ ሂደታችን የመጣ በመሆኑ ምንም አልተከናወነም፡፡ ሲዳማ፣ሀድያ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ወላይታ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ጋሞ

ጎፋ፤ ደ/ኦሞ፤ ሰገን አ/ባቢ ሕዝቦች እና ስልጤ ዞኖች፤ ሀዋሳ ከተማ ፤ ኮንታ እና የም ልዩ ወረዳ ድጋፍና ክትትል ያደረጉ ሲሆን ቀሪዎቹ መዋቅሮች ምንም ያላከናወኑ ናቸው፡፡

14) የብር 462,336,170 የሀገር ወስጥ የገበያ እድል በማመቻቸት 5567 ተቋማትን እና 22684 ወንድ 20348 ሴት በድምሩ 43033 አንቀሳቃሽ ወጣቶች እና ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ በእቅድ ተይዞ ብር **341,867,859** የሀገር ወስጥ የገበያ እድል ለ**4929** ተቋማት እና ለ **28628** ወንድ **11134** ሴት በድምሩ **39762** አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ በብር **73.9%**፣ በተቋም 88.5% ሲሆን በአንቀሳቃሽ **92%** በመሆን ተከናወኗል፡፡ በተፈጠረ ገበያ በጣም ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡት ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሃድያ፣ ወላይታ፣ ከምባታ ጠምባሮ ዞኖችና ሃዋሳ ከተማ ሲሆኑ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ከፋና ጋሞጎፋ ዞኖችና ኮንታ ልዩ ወረዳ ናቸው፡፡ ቤንች ማጂ፣ ሸካና ሰገን አካባቢ ህዝቦችና ሃላባ ልዩ አጥጋቢ አፈጻጸም ያላቸው ሲሆን ዳወሮ፣ ጌድኦ፣ የምና ባስኬቶ ልዩ ወረዳዎች ዝቅተኛ አፈጻጸም ላይ ይገኛሉ፡፡

15) በክልልና በየደረጃው በሚገኙ መዋቅሮች በቁጥር 54 ባዛርና ኤግዚቢሽን በማዘጋጀት የብር 14,452,054 የገበያ ትስስር ለመፍጠር በእቅድ በተያዘው መሰረት በቁጥር 38 ባዛርና ኤግዚቢሽን ተካሂዶ የብር 14,866,876 የገበያ እድል መፍጠር ተችሏል አፈጻጸሙ በቅደም ተከተል 70% እና 103% በመሆን ተከናወኗል፡፡ በተፈጠረ ገበያ በጣም ከፍተኛ ወጤት ያስመዘገበ ዞን ከምባታ ጠምባሮ ሲሆን ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገበ ሃድያ ዞን ነው፣ አጥጋቢ አፈጻጸም ያስመዘገቡ የሌሉ ሲሆን ጉራጌ፣ ስልጤና ከፋ ዞኖች፣ ሃዋሳ ከተማና ኮንታ ልዩ ወረዳ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያሳዩ ናቸው፡፡ ጋሞጎፋ፣ ደበብ ኦሞ፣ ሰገን አካባቢ ህዝቦች፣ ዳወሮ፣ ቤንች ማጂ፣ ሸካ፣ ሲዳማ፣ ጌዲኦና ወላይታ ዞኖችና ሀላባ፣ ባስኬቶና ኮንታ ልዩ ወረዳዎች ምንም ወጤት ያላስመዘገቡ መዋቅሮች ናቸው፡፡

16) በሀገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ባዛርና ኤግዚቢሽን በቁጥር 20 ተቋማት የብር 402,695 የገበያ ትስስር ለመፍጠር በእቅድ በተያዘው መሰረት 30 ተቋማት የተሳተፉ ሲሆን የብር 777,884 የገበያ ትስስር ተፈጥሯል፡፡ አፈጻጸሙ ከተቋም አንጻር 150 % እና ከተፈጠረ የገበያ ትስስር አንጻር 193 % በመሆን ተከናወናል፡፡ በተፈጠረ የገበያ ትስስር ከምባታ ጠምባሮ ዞን በጣም ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገበ ሲሆን ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡት ሃድያ፣ ጉራጌ፣ ጋሞጎፋ፣ ስልጤ፣ ወላይታና ሀዋሳ ከተማ ሲሆኑ አጥጋቢ አፈጻጸም ያላቸው ደቡብ ኦሞ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ጌዲኦ፣ ባስኬቶ፣ ኮንታ፣ ሰገን ህዝቦች፣ ቤንች ማጂ፣ ካፋና ሸካ መዋቅሮች ናቸው፡፡ ሲዳማ ጌደኦ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ወላይታ፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀድያ፣ ቤንች ማጂ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ጋሞጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ሰገን አካባቢ ህዝቦች፣ ዳወሮ ዞኖችና ሀላባ፣ ኮንታ፣ ባስኬቶ፣ የም ልዩ ወረዳዎች ምንም ያላከናወኑ መዋቅሮች ናቸው፡፡

17) የገበያ እድል ለማስፋት የሚያግዙ 4 የግብይት ስርአቶች በስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ በማድረግ በሀገር ወስጥና በወጪ ሃገር ገበያ በአወት ሶርሲንግ ብር 270,909,393፣ በንዑስ ተቋራጭ ብር 138,129,028፣ በአወት ግሮዊንግ ብር 44,270,637፣ በፍራአንቻይዚንግ ብር 26,800,000፣ በድምሩ 473,109,057 የገበያ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በአወት ሶርሲንግ ብር 359,650,845 (133%)፣ በንዑስ ተቋራጭ ብር 120,345,986 (87%) እና በአወት ግሮዊንግ ብር 34,295,630(77%)፣ በፍፍራንቻይዚንግ 948,499 በድምሩ 515,240,960 (98%) የገበያ እድል መፍጠር ተችላል፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ወላይታ፣ ጋሞጎፋ፣ ስልጤ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ሲዳማ፣ ዳወሮ ዞኖችና ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ሲሆኑ አጥጋቢ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ደግሞ ጉራጌና ቤ/ማጂ ዞኖች

እንዲሁም ሀላባ ልዩ ወረዳ ናቸው፡፡ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸው ደ/አሞ፣ ጌደኦ፣ ሰገን፣ ካፋና ሸካ ዞኖች እንዲሁም የም፣ ባስኬቶና ኮንታ ልዩ ወረዳዎች ናቸው፡፡

18) በቁጥር 21 ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የምርት ጥራት ፍተሻ እንዲደረግላቸው ለማድረግ በዕቅድ ተይዞ **17** የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተቋማት የምርት ጥራት ፍተሻ ማድረግ ተችሏል አፈጻጸሙ **81**% በመሆን ተከናውኗል ፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ስልጤ፣ጋ/ጎፋና ከምባታ ጠምባሮ ዞኖችና ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ሲሆኑ ጉራጌ ዞን አጥጋቢ ወጤት አስመዝግቧል፡፡ ሀድያ፣ቤንች ማጂ፣ከፋ፣ሸካ፣ሰገን አካባቢ ህዝቦች፣ጌደኦ፣ሲዳማ፣ዳወሮ ዞኖችና ኮንታ፣ባስኬቶና የም ልዩ ወረዳዎች ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ናቸው፡፡

19) በቁጥር 17 ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች በፌደራል ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ምርት ማሳያና መሸጫ አምፓሪየም ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የብር 1,680,000 የገበያ ትስስር ለመፍጠር በእቅድ በተያዘው ማስረት በዚህ በያዝነው በጀት አመት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተቋማት ወደ አምፖሪየም የገቡ የሉም፡፡ ምክንያቱም በ2008 በጀት ዓመት ወደ አምፖርዬም የገቡ 12 ማኑፋክቸሪንግ ተቋማት ጨርሰው ባለመውጣታቸው በ2009 በጀት ዓመት ሊገቡ አልቻሉም፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ሲል ለገቡት 12 ተቋማት የብር 786,370 የገበያ እድል ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡ አፈጻጸሙ በመቶኛ ሲታይ ከተቋማት ቁጥር አንጻር 74 በመቶ ሲሆን ከተፈጠረ የገበያ ትስስር አንጻር ደግሞ 47 በመቶ ይሆናል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል የቻለበት ምክንያት በበጀት አመቱ ከፌደራል ኢንዱስትሪያሊስቶች እንዲገቡ ፈቃድ ባለማስጠቱና በ2008 በጀት ዓመት ወደ አምፖርዬም የገቡት ባለመውጣታቸው ከክልሉ የተማለሙ ቢኖሩም ማስገባት ባለመቻሉ ነው፡፡

20) ለብረታብረት የ60,000 ዩ ኤስ ዶላር፣ለእንጨት 60,000 ዩ ኤስ ዶላር፣ለአግሮፕሮሰሲንግ 272,153 ዩኤስ ዶላር፣ ለጨርቃጨርቅና አልባሳት 917,270 ዩ ኤስ ዶላር፣ ለቆዳና ቆዳ ወጤቶች 450 ዩ ኤስ ዶላር በድምሩ **1,979,423** ዩ ኤስ ዶላር የወጪ ሀገር የገበያ እድል ለማግኘት ታቅዶ በአግሮፕሮሰሲንግ **470,321.18** ዩ ኤስ ዶላር፣ በጨርቃጨርቅና አልባሳት **102,465** ዩ ኤስ ዶላር በድምሩ **572,786.18** ዩ ኤስ ዶላር የወጪ ሀገር የገበያ እድል ተማኝቷል፣ አፈጻጸሙ **29**% በመሆን ተከናውኗል፡፡ በተፈጠረ ገበያ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ከፋ፣ ጋሞ ጎፋ ዞንና ሀዋሳ ከተማ ሲሆኑ ደቡብ ኦሞ፣ ሰገን አካባቢ ህዝቦች፣ ሸካ፣ ሲዳማ፣ ጌደኦ፣ ከምባታ ጠምባሮ፣ ዳወሮ፣ ጉራጌ፣ ቤንች ማጂ፣ ስልጤ፣ ባስኬቶ፣ ኮንታና የም ልዩ ወረዳዎች ምንም ያላከናወኑ መቀቅሮች ናቸው፡፡ በተቋም ደረጃ በወጪ የገበያ 40 ተቋማትን ተጠቃሚ ለማድረግ በእቅድ በተያዘው ማስረት **10** ተቋማትን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል አፈጻጸሙ **25**% ነው፡፡

የውጭ ገበያ ተሳትፎ ሲታይ እስካሁን እየተሳተፉ ያሉ ተቋማት ቁጥር አነስተኛ ሲሆን ምርቶቻቸው በጥራትና በማጠን እንዲሁም በዋጋ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከማስቻል አንጻር ወስንነቶች በመኖራቸውና በቆዳው ዘርፍ ወደ ውጭ ገበያ ለማግባት የሚፈልጉና በምርት ጥራታቸው ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ የማኑፋክቸሪንግ ተቋማት ያሉ ቢሆንም ጥራት ያለው ጥሬ ዕቃ በሚፈልጉት ማጠንና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት ባለመቻላቸው የውጭ ገበያውን መቀላቀል ሳይችሉ በመቅረታቸው፣ እንዲሁም ከዚህ ቀደም የውጭ ገበያ በማስተፍ የሚታወቀው ጃኖ የባህል አልባሳት ኢንዱስትሪ የጥጥ መፍተል ሰራውን አወትሶርስ የሚያደርግላቸው የአካባቢ ሴቶች በተለያዩ ምክንያቶች ሊሰሩለት ባለመቻላቸው ምክንያት ከኤክስፖርት ገበያ በመውጣቱ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል ችሏል፡፡ ይሁንና የአፒኔክ ሚ ማቅነባበሪያ ኢንዱስሪ እንዲሁም በሀዋሳ ከተማ (አበባ ባህላዊ አልባሳት እና በሥጅ ሀለት ኢንዱስትሪዎችን በማቅፍ፤ ጸሀይ ጨ/ጨ/አልባሳት፣ ኢትዮ ኔት ጨ/ጨ/አልባሳት፣ ሚኪዳ ጥበብ

ጨ/ጨ/አልባሳት)፤ በጋሞ ጎፋ ዞን የሚገኙ ጃኖ ባህላዊ አልባሳት፣ በርታ ሞሬንጋና ጋሞ ጥበብ የባህላ አልባሳት በማምረት ላይ ያሉ ወስን ኢንዱስትሪዎች ባደረጉት የወጭ ግብይት አፈጻጸሙ ሊመዘገብ ችሏል፡፡

21) በቁጥር 267 ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተቋማት የሚያስፈልጉ ግብአቶች /ጥሬ ዕቃዎች ሚረጃ በማሰባሰብና ጥናት ለማድረግ በእቅድ በተያዘው ማሰረት 155 ተቋማትን ተጠቃሚ ሆነዋል አፈጻጸሙም 58% በመሆን ተከናወናል፡፡ ከፍተኛ ወጤት ያስመዘገቡ ጋሞጎፋ፣ ከፋ፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፤ ሀድያ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ዞኖችና ሃዋሳ ከተማና የም ልዩ ወረዳ ሲሆኑሸካ ዞን አጥጋቢ ወጤት አስመዝግቧል፡፡ ዝቅተኛ ወጤት ያስመዘገቡ ሃላባና የም ልዩ ወረዳ ሲሆኑ ምንም ያላከናወኑ ሲዳሞ፣ ጌዴኦ፣ ወላይታ፣ ዳወሮ፣ ሰገን አካባቢ ህዝቦች፣ ቤ/ማጂ ዞኖችና ኮንታና ባስኬቶ ልዩ ወረዳዎች ናቸው፡፡

22) በቁጥር 27 የተለያዩ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ለ**485** አንቀሳቃሾች በማስፋት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በእቅድ በተያዘው ማሰረት **34** ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር ለ**452** አንቀሳቃሾች እንዲሰፋ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙም በቅደም ተከተል **126%** እና **93%** በመሆን ተከናወናል፡፡ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራን በተመለከተ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ጋሞጎፋ፣ ከፋ፣ ወላይታ፣ ሀድያ፣ ሲዳሞ፣ ከምባታ ጠምባሮ ዞኖችና ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ሲሆኑአጥጋቢ አፈጻጸም ያስመዘገበ ጉራጌ፣ ስልጤ፤ ዳወሮና ሸካ ዞኖችናሀላባ ልዩ ወረዳ ሲሆኑ፡፡ ቤንች ማጂ፣ጌደኦ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖችና የም፣ ኮንት፣ ባስኬቶ ልዩ ወረዳዎች ምንም ያላከናወኑ መዋቅሮች ናቸው፡፡

23) ከታችኛው መዋቅር ለተሚጠቱ በቁጥር **498** ሞዴል ተቋማት ዕወቅና ለማሰጠት በእቅድ በተያዘው ማሰረት **601** ሞዴል ተቋማት እወቅና ተሰጥቷል አፈጻጸሙም 121 % በመሆን ተከናውኗል፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ስልጤ፤ ሀድያ፣ ከፋ፣ ዳወሮ፣ ወላይታ፣ ሲዳሞ፣ ከምባታ ጠምባሮ ዞኖችናሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ሲሆኑ ባስኬቶ ልዩ ወረዳ አጥጋቢ ወጤት አስመዝግቧል፡፡ጉራጌ፣ ሸካ፣ጋ/ጎፋና ሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞን ዝቅተኛ አፈጻጸም ሲኖራቸው ጌደኦ፣ ቤ/ማጂና ሸካ ዞኖች እንዲሁም ኮንታ፣ ሀላባማ የም ለረዩ ወረዳዎች ምንም ያላከናወኑ መዋቅሮች ናቸው፡፡

24) የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ተቋማት ዕድገት ደረጃ እወቅና ማስጠትን በተመለከተ በቁጥር 597 ከጀማሪ ጥቃቅን ወደ ታዳጊ ጥቃቅን፣ 395 ከታዳጊ ጥቃቅን ወደ ጥቃቅን፣ 239 ከበቃ ጥቃቅን ወደ ጀማሪ አነስተኛ፣ 197 ከጀማሪ አነስተኛ ወደ ታዳጊ አነስተኛ፣ 90 ከታዳጊ አነስተኛ ወደ መብቃት፣ 51 ከበቃ አነስተኛ ወደ ታዳጊ መካከለኛ በማሸጋገርዕወቅና የማስጠት እና 89 ከሌሎች ዘርፎች ወደ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በድምሩ 1,661 ለማሸጋገር በእቅድ በተያዘው ማሰረት 796(133%) ከጀማሪ ጥቃቅን ወደ ታዳጊ ጥቃቅን፣ 415(105%) ከታዳጊ ጥቃቅን ወደ ጥቃቅን፤ 364(152%) ከበቃ ጥቃቅን ወደ ጀማሪ አነስተኛ፣ 290(147%) ከጀማሪ አነስተኛ ወደ ታዳጊ አነስተኛ፣ 114(127%) ከታዳጊ አነስተኛ ወደ መብቃት፣ 78(153%) ከበቃ አነስተኛ ወደ ታዳጊ መካከለኛ በማሸጋገር ዕወቅና የማስጠት እና 106(119%) ከሌሎች ዘርፎች ወደ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ማሸጋገር በድምሩ 2163 ተቋማት የተሸጋገሩ ሲሆን አፈጻጸሙ 130% ነው፡፡ ከፍተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡት ወላይታ፣ ስልጤ፤ ሃድያ፣ ከምባታ ጠንባሮና ሲዳማ ዞኖችና የም እና ሃላባ ልዩ ወረዳዎች ሲሆኑ አጥጋቢ አፈጻጸም ያስመዘገበ ዳወሮ፣ከፋ፣ ጉራጌና ጋ/ጎፋ፣ ቤንች ማጂና ደ/ኦሞ ዞኖችና ሀዋሳ ከተማ ኮንታ፣ ባስኬቶ ልዩ ወረዳዎች ናቸው፡፡ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡሰገን አካባቢ ህዝቦችና ጌደኦ ዞኖች እንዲሁም ባስኬቶ ልዩ ወረዳ ናቸው፡፡ ለአፈጻጸሙ ከፍ ማለት በሩብ ዓመቱ የተደረገው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ቆጠራ በተለይም ወደ ተግባር ከገቡ በኋላ

በቂ ክትትል በማጣታቸዉና ካፒታላቸዉን የደበቁ ኢንዱስትሪያሊስቶችን በአግባቡ ተደራሽ ማድረግ በመቻሉ ነዉ፡፡

25) በቁጥር 29,301 ወንድ እና 26,956 ሴት በድምሩ 56,257 አንቀሳቃሾችን ሁሉ አቀፍ የሚጃ አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ በእቅድ በተያዘው መሰረት **36,245** ወንዶች እና **22,524** ሴቶች በድምሩ **58,769** አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ መሆን ችለዋል አፈጻጸሙ **104**% በመሆን ተከናወናል፡፡ ለተጠቃሚዎች ከተሰጡ የሚጃ አገልግሎቶች ወስጥ የገበያ ሚጃ፣ የማርያ ሊዝ አገልግሎት፣የማርያ ሊዝ ቁጠበ በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆኑ አፈጻጸሙ ከፍ ሊል የቻለበት ምክንያት በማነበርም ሆነ በግል በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ መሳተፍ የሚፈልጉ ተዋንያን ቁጥር እየጨመ ማማጣትና በወስን ሚሊኩ የማሽነሪ አቅርቦት በመጀመሩ መሆኑን ማንዘብ ተችሏል ፡፡

26) በ 147 የማኑፋክቸርንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በሚገኙ ተቋማት የካይዘን ትግበራ በመደገፍ በ20% ብክነትን ለመቀነስ በእቅድ ተይዞ **134** ማከናወን ተችላል አፈጻጸሙ **91**% በመሆን ተከናወናል፡፡

27) ከካይዘን ኢንስቲትዩት ጋር በቅንጅት በመሥራት ለ5 የአሰልጣኞች ስልጠና እና ለ144 የባለሙያዎች የካይዘን ስራ አመራር ስልጠና ለማስጠት ታቅዶ ለ 23 የአሰልጣኞች ስልጠ እና ለ74 የባለሙያዎች የካይዘን ስራ አመራር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ይሁንና ለአሰልጣኞችም ሆነ ለፈጻሚ ባለሙያዎች ስልጠናው የተሰጠው በካይዘን ኢንስቲቲዩት ሳይሆን በየመዋቅሩ ባሉ የቴ/ሙያ ተቋማት ሲሆን በቀጣይ በቢሮአችን አማቻችነት በካይዘን ኢንስቲቲተዩት ስልጠናው እንዲሰጥ የሚማቻች ይሆናል፡፡

28) ሥርዓተ-ጾታን በሥራ ሂደቱ ሥራዎች በማካተት ተጠቃሚ ለማድረግ 100ለማካተት በተያዘው ዕቅድ መሰረት የሴቶች ተሳትፎ በአማካይ 60 በመቶ ደርሷል፡፡የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመካላከል ሥራዎችን ከልማት ዕቅዶች አንጻር ሜይንስትሪም ለማድረግ 80% በእቅድ በተያዘው መሰረት ማከናወን ተችሏል፡፡ ይህም በየተቋማቱ 2 በመቶ በጀት እንዲመደብ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት በጀቱ ተመድቦ ተግባር ላይ እየዋለ ነዉ፡፡

29) 19ኙም መዋቅሮች በየዘኑ በሚገኙ ወረዳዎችና ከተሞችን እስከ ሩብ ዓመቱ 3 ዙር የእቅድ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ **100**% ማከናወን ተችላል፡፡

30) የዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርት ማዘጋጀትና ግብረ-መልስ መስጠት በቁጥር 8 ታቅዶ 8 ተከናወኗል፡፡ አፈጻጸሙ 100% ነዉ፡፡

## ያጋጠሙ ችግሮች

- ከሊዝ ማሽን አቅርቦት ጋር ተያይዞ ኢንተርፕራይዞች ለስራ የሚውል ገንዘብ ለቁጠበ አስይዘው ማሽኑ በወቅቱ አለመማጣቱ በኢንተርፕራዞች ላይ ቅሬታ በስፋት እንዲነሳ ማድረጉ፣

- የቴ/ሙያ ኮሌጆች የስልጠና ማእከ ወሰን መሆኑና በተለይም በአግሮ ፕሮሰሲንግና በቆዳ ሥራ ን/ዘርፎች የቴክኖሎጂና የክህሎት ድጋፍ የሚሰጡ ቴ/ሙያ ተቋማት አነስተኛ መሆናቸው፣
- በስራ ሂደቱ ለሚገኙ ነባርና አዳዲስ ባለሙያዎች የክህሎት ክፍተት እና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች አለማሰጠቱ፣
- ከክልል ጀምሮ የኮምፒውተርና ተሽከርካሪ እጥረት በከፍተኛ ሁኔታ በየደረጃው ባሉ መዋቅሮች መኖሩ
- ከታችኛው መዋቅር የሚላኩ ሪፖርቶች ከክልሉ በተላከው የሪፖርት ፎርማት ማሰረት ተሟልተውና ጊዜውን ጠብቀው ያለመላክ፣
- የስራ ሂደቱ በአዲስ ከተዋቀረ ጀምሮ የሰው ሀይል ለማሟላት ጥረት ቢያደርግም በታችኛው መዋቅሮች በዘርፉ የተሚዚ የሰው ሀይል በበቂ ሁኔታ ያለመኖሩ፤

**ማጠቃለያ**

የክልሉ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ በስደስት ወሩ የ2009 በጀት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ አፈፃጸምን በተገቢው በጥልቀት በማምገምና በተጨባጭ ሊተገበር ይቻላሉ ተብለው የተገመቱ ግቦችን በአግባቡ በማካለስና በማቀድ ወደ ተግባራዊ ሥራ ወስጥ መግባት ተችሏል፡፡ ይህ በክልል ደረጃ ብቻ ሳይሆን በየደረጃወም ባሉ መዋቅሮች ጭምር ጥሩ የዝግጅት ምዕራፍ ተደርጎ ሥራ ወስጥ የተገባበት በጀት ዓመት ነበር፡፡ ይህም በመሆኑ የመጀመሪያ መንፈቅ አፈፃጸም የተሻለ እንደነበር ተገምግሟል፡፡

ሆኖም እንደ ሀገር በተከሰቱ የተለያዩ ችግሮች ምክንያት ዕቅዱ በተጀመረበት ፍጥነት ሊጓዝ አልቻለም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ እስከ ማከረም 30/2009 ይጠናቀቃል የተባለው የአቅም ግንባታ ሥራ አለመተግበር በአሰራር ግልጽነት መፍጠር ባለመቻሉ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን እስከ አንድ ሚሊዮን እንዲደራጅ በተቀማጠው አቅጣጫ ማስረት የተወሰኑ መዋቅሮች ተግባራዊ ለማድረግ የሞከሩ ቢሆንም በርካቶች ይህንን በተሟላ ሁኔታ መተግበር ያለመቻላቸው የዘርፉን ሥራ ቀላል በማይባል ደረጃ ጎቶታል፡፡

በመሆኑም አጠቃላይ የስራ ሂደቱ ሚዛናዊ አፈፃጸም ሲሰላ የተሸለ ዉጤት መመዝገቡን ሚያዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥለው 3 ወር በተለይም በ4ኛው ሩብ ዓመት ላይ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ትልቅ ርብርብ ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ካሁኑ ማስረታዊ ችግሮች አፈታት ላይ ርብርብ ማድረግ ግድ ይላል፡፡